Week 20

Grade 2

# መስታወት



Leveled

# መስታወት

Leveled | Grade 2 | Week 20



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children)፣ በትምህርት ሚኒስቴር እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ ታተመ::

2008 ዓ.ም.

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*




የምግብ ዝግጅት ውድድሩ ተጀምሯል።



የምግብ ባለሙያዎች ሽርጉድ ይላሉ።



መስታወት ስጋ ወጡን በሽክላድስት ሰራች::



አትክልት በብረትድስት ሰራች።



መስታወት ሽሮ ወጥ ለመስራት ፈለገች።



የሽሮ ወጥ መስሪያ ሽክላድስት አጣች፡፡




ጓደኛዋን ጠየቀችው:: “ውድድር
መሆኑን ረሳሽው?” አላት::



መስታወት “ምን አለበት?” አለችው::



ጓደኛዋም “ሽክላድስቴን ላንቺ ሰጥቼ በምን ልሰራ ነው?” አላት፡፡



መስታወትም “ልክ ነህ፤ መጀመሪያ ማቅረብ ነበረብኝ” አለችው።



ጓደኛዋም “ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ ሆነብሽ እኮ!” አላት፡፡



መስታወትም “ችግር ብልሃትን
ይፈጥራል፤ ሽሮ ወጡን
በመጥበሻ እሰራዋለሁ” አለችና
ከልቧ ሳቀች፡፡